የሰ/መ/ቁ. 27959

ኅዳር 03 ቀን 2000

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢት/ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት - ነ/ፈጅ ታደሰ በቀለ

ተጠሪ፡- አቶ አሊ መሐመድ አሊ - ቀረበ፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረቡት ተጠሪ ስራ ላይ ላልነበሩበትና በክርክር ላይ ለነበሩበት የ5 ዓመት የአመት እረፍት እንዲሠጣቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ከሥራ አሠናብቷቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ክስ መስርተው በክርክር ላይ ለነበሩበት ጊዜ ያልተሠጣቸው የአመት እረፍት እንዲሠጣቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ሁለት አመት ያለፈው የአመት እረፍት ሊሠጣቸው እንደማይገባና ስራ ላይ ላልነበሩበት ጊዜ የአመት እረፍት ሊሠጣቸው እንደማይገባ ተከራክሯል፡፡ ወረዳ ፍ/ቤቱም ተጠሪ ክርክር ላይ ለነበሩበት ጊዜ ይርጋው የሚቋረጥ በመሆኑ ከ1991 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም. ያለው የአመት እረፍት እንዲሠጣቸው በማለት ወስኗል፡፡ የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ ስራ ላይ ላልነበሩበት ጊዜ የአመት እረፍት እንዲሠጣቸው መወሰኑ አግባብ መሆን አለመሆኑ፣ነው ቢባል እንኳን 2 ዓመት ያለፈው የአመት እረፍት ሊሠጣቸው የሚገባ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሠበት ችሎት እንዲቀርብ አድርጎ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡



ከመዝገቡ እንደተረዳነው ተጠሪ ከስራ ተሠናብተው ስለነበር ወደ ሥራ እንዲመለሱ ክስ መስርተው ተወስኖላቸው ወደ ስራ ተመልሰዋል፡፡ አሁን ክስ ያቀረቡት ከስራ ተሠናብተው ለነበሩበትና በክርክር ላይ ለነበሩበት ጊዜ ያልወሰዱት የአመት እረፍት እንዲሰጣቸው ነው፡፡

በመሠረቱ የሣምንት ወይም የአመት እረፍት የሚሠጠውም ሆነ በቀን የተወሰነ ሠዓት ብቻ እንዲሠራ ሕጉ የሚያስገድደው ሠራተኛው በሥራ የደከመ አእምሮውንና አካሉን በማሣረፍ አካላዊና አእምሯዊ ጤንነቱን በመጠበቅ የሥራ ውጤታማነቱ እንዲጨምር ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሠራተኛ የሣምንት ወይም የአመት እረፍት የማግኘት መብት ሊኖረው የሚችለው በሥራ ገበታው ላይ ተገኝቶ ሥራ ለሠራበት ጊዜ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪ የአመት እረፍት እንዲሠጠው እየጠየቀ ያለው ስራ ላይ ላልነበረበት ጊዜ በመሆኑ እና የሕጉም አላማ ይህ ባለመሆኑ የተጠሪ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የአመት እረፍት በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 79/5/ የአመት ፈቃድ ከሚቀጥለው ሁለት አመት በላይ ሊተላለፍ እንደማይችል ስለሚያመለክት ሁለት አመት ያለፈው የአመት ፈቃድ ለተጠሪ እንዲሠጠው የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የጉቶ ጊዳ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03144 በሚያዝያ 18 ቀን 1998 የሠጠው እንዲሁም የምስ/ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10075 በኅዳር 28 ቀን 1999 ዓ.ም. የሠጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ስራ ላይ ላልነበሩበትና በክርክር ላይ ለቆዩበት ጊዜ የአመት እረፍት ሊሠጣቸው አይገባም፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ